# እግዚአብሔር ያጥናሽ እማማዬ

የሕብረተ-ሰብ ማማ ሆነሽ፣

ያም ሆኖ፣ በችግር በመከራ እየተጠበስሽ፣

ልጆችሽን ጥረሽ ግረሽ

ጥረሽ ግረሽ አሳድገሽ፣

ከትንሽ እስከ ትልቅ፣

ከሊቅ እስከደቂቅ፣

በአካባቢሽ ኮልኩለሽ፣

ለፈጣሪ ክብሩ ይስፉ፣

ከእንግዲህስ ደርሰውልኛል፣

ከመከራ ከችግር ያወጡኛል፣

ለእኔም፣

ለሀገር፣ ለወገንም

አይኟችሁ ባይ ይሆኑናል፤

ስትይ፣

እማማዬ፣ የእኛ እማማ፣

ኧ! ብትን፣ ብትንን አሉልሽ፣

ላልታሰበ፣ ላልታለመ መከራ ተዳረጉልሽ።

ዜግነታዊ ክብራቸውን አጥተው፣

ተገፎ ሰብ-አዊ መብታቸው፣ ነፃነታቸው፣

ተዳረጉ ለባሰ ስቃይ፣ ለመከራ ለስደት፣

ይባስ ብሎም በየሄዱበት::

ክብራቸው ተገፎ ተላበሱ የጥቁር ካባ ውርደት፣
ቀረቡ ለሰይጣን መልዕክተኞች ለሰው ፍሪዳነት።
በጨካኝ የባዕድ እጅ ወድቀው፣
አንገታቸው ተቀልቶ በሰይፍ ተሰይፈው፣
በጥይት ናዳ ተፈረካክሶ ጭንቅላታቸው፣
በየቦታው ተፈነጣጥቆ እንደጅረት ሲንቆረቆር፣ ከባህር ሲቀላቀል ደማቸው፣
እዚህ እዚያ፣ ወዲህ ወዲያ፣  ወዳድቆ ተለያይቶ አካላቸው፣

እግዚኦ ፈጣሪያችን፣
አቤቱ አምላካችን፣
ምኑን ሰማ ጆሯችን?
ምኑንስ አዩ ዓይናችን?

እጅ ከዎርች ታስረው፣
በጎማ ተቀይደው፣
ቤንዚን ተርከፍክፎባቸው፣
ሲነዱ፣ ሲቀቀሉ፣
በእሳት ሲጋዩ ሲቃጠሉ፣
ሰማን፤ አየናቸው።

እግዚኦ ፈጣሪያችን፣
አቤቱ አምላካችን?
ምኑን ሰማ ጆሯችን፣
ምኑንስ አዩ ዓይናችን?

ጀልባም ሲነጉድ ይዟቸው፣

ለባህር አውሬ ቀለብ ሲዳርጋቸው፣

በበረሃም የመስክ አውሬ ሲቀራመታቸው፣

ወበከንቱ ሲሆኑ ሲጠፉ ደብዛቸው፣

አገር ወገን እንደሌላቸው፣

በእትብት ምድራቸው በወግ በማዕረጉ አፈር ሳናለብሳቸው፣

የበረሃውና የባህሩ አውሬ **ተቀራመታቸው፤**

**እዎ! ተቀራመታቸው፤** በላቸው፤

ተቃጠሉ፤ ዶግ-አመድ ሆኑ በጭስ በነኑ ወደ ሰማየ-ሰማያት ቤታቸው።

እግዚኦ ፈጣሪያችን፣

አቤቱ አምላካችን፣

ምኑን ሰማ ጆሯችን?

ምኑንስ አዬ ዓይናችን?

አይ እማማዬ እናታችን፣

እስተንፋሳችን፣ ደም፣ ሥጋ፣ አጥንታችን፣

ብዙ ብዙ መከራ አሳልፈሻል ይሁንና፣

አሁን አሁን በታሪክ ባላየሽው፣

ለዘመናት ባልሰማሽው፣

በዓይነቱ በተለዬ የመከራ ስቃይ ተውጠሽ፤

ወደመሪርር ኃዘን መቀመቅ ወረድሽ።

የደረሰው ኃዘን ከሰው አቅም በላይ ነውና፣

እማዬ፣ እሱ አንድዬ ብርታቱን ይስጥሽ፤

እንዲሁም ለኛ ለልጆችሽ።

እግዚኦ ፈጣሪያችን፣
አቤቱ አምላካችን፣
ምኑን ሰማ ጆሯችን?
ምኑንስ አዬ ዓይናችን?

**ብርታቱን ይስጠን!**

**መታሰቢነቱ**

በየመን፣ በደቡብ አፍሪካ፣ በሊቢያና ሌሎች የአረብ አገሮች

በግፍ እየተሰቃዩና እየተገደሉ ላሉ ወገኖቻችን።

ከየትናየት አገር

መጋቢት 2007